# ከእግዚአብሔር ጋር የጠለቀ ግንኙነት ማድረግ

## ክፍል ፩

## <u>እግዚአብሔርን የምናመሰግንበት ምክንያት አለን</u>

ዳዊት በተለያየ መልኩ ከሞት አፋፍ እግዚአብሔር ያዳነው ሰው ነው። በእረኝነት ላይ እያለ ከአንበሳና ከድብ ጠብቆታል፣ ከሳኦልም ጦርና ማሳደድ አድኖታል፣ ከዚህም በተጨማሪ ሳኦልን በመፍራት ወደ ጌት በሸሸ ጊዜ የጌት ንጉስ አንኩስም ሊገለው እንደፈለገ ተረድቶ እራሱን እንደ እብድ አድርጎ በማቅረቡ እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ እንዳስመለጠው በማሰብ ጥልቅ የሆነ ምስጋና ለማቅረብ፣ ሌሎችንም ከእርሱ ጋር ተባብረው ለዚህ ታላቅ ለሆነ ጌታ ምስጋና ለማቅረብ ጥሪ በማድረግ ዳዊት እንዲህ ይላል፡-

*"እግዚአብሔርን ሁልጊዜ አባርከዋለሁ፥ ምስጋናውንም ዘወትር በአፌ ነው።*

*ነፍሴ በእግዚአብሔር ትከብራለች፥ ገሮችም ሰምተው ደስ ይላቸዋል።*

*እግዚአብሔርን ከእኔ ጋር ታላቅ አድርጉት፥ በአንድነትም ስሙን ከፍ ከፍ እናድርግ።"*

*(መዝ. 34፡1-3)*

በእንዲህ አይነት አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ያለፈ ዳዊት፥ እግዚአብሔር በእርግጥ ፀሎትን የሚሰማ የቅርብ አምላክ እንጂ የሩቅ እንዳልሆነ ተረዳ፣ ይሄም ሁኔታ ከአምላኩ ጋር ያለውን ግንኙነት የጠበቀ እንዲሆን እንዳደረገለት ሲናገር፡-

*"እግዚአብሔርን ፈለግሁት መለሰልኝም፥ ከመከራዬም ሁሉ አዳነኝ።*

*ወደ እርሱ ቅረቡ ያበራላችሁማል፥ ፊታችሁም አያፍርም።*

*ይህ ችግረኛ ጮኸ፥ እግዚአብሔርም ሰማው፥ ከመከራውም ሁሉ አዳነው።*

*የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል፥ ያድናቸውማል።*

*(መዝ. 34፡4-7)"*

እኛም እያንዳንዳችን በብዙ በሚያስፈሩ ሁኔታዎች ውስጥ ብናልፍም እንኳን፣ እነዚያ ሁኔታዎች ስላላጠፉን ይልቁንም ወደ እርሱ ስንጮህ የሰማንንና ከራሱም ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖረን ያደረገንን ጌታ ከዘማሪው እንዲሁም ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ሆነን እለት እለት ምስጋና ልናቀርብለት ያስፈልገናል።